# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 2 ቁጥር 69 ታህሳስ 21 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ


# የምርጫ ጊዜ ሰሌዳ
# እና
# የሁለት ቀን ምርጫ



# ቆይታ

## < < መንግሥት እንደ በፊቱ ዓይነት ምርጫ አደርጋለሁ ካለ ራሱን ችግር ውስጥ ይከታል፡፡ > >

### ከውሰር እንድሪስ (የኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ጸሀፊ)

ከውሰር እንድሪስ የምርጫ ዝግጅቱን በከፍተኛ ሁኔታ በማስተባበር በሚገኘው የኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ውስጥ ጸሐፊ ናቸው፡፡ የዚህ ሳምንት የዜጎች መድረክ የ «ቆይታ» አምድ እንግዳ ናቸው፡፡የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ እጩ የማሳወቂያ፣የቅስቀሳ እና የምርጫ ቀን ቆርጦ ማስቀመጡን በማስመልከት ከዜጎች መድረክ ጋር ተከታዩን ውይይት አድርገዋል፡፡እንድታነቡት ጋብዘንዎታል፡፡ መልካም ንባብ!



*የዘንድሮ ምርጫ ምን ዓይነት ምርጫ ይሆናል ብለን እንጠብቅ?*

በያዝነው 2013 ዓ.ም የምናካሄደው ሀገር አቀፉ ምርጫ እንደማንኛውም ዓይነት ምርጫ አይደለም፡፡ ታሪካዊና ሀገራዊ ፋይዳ አለው ብለን እናስባለን፡፡ የሕዝብ ድምፅ በአግባቡ ሊታይበት የሚችል ምርጫ ነው፡፡ከዚህ በፊት የሕዝብን ፍላጎት ለማስተናገድ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት አላሳዩም ወይም ፍላጎት ያላቸው ይመስሉና ውጤቱን ይቀለብሱታል፡፡ በዘንድሮ ምርጫ ለመጀመሪያ ጊዜ የሕዝብ ድምፅ ዋጋ ያገኛል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

በቦርዱ የሚገለጸው ሀገራዊና ክልላዊ ውጤት ፓርቲዎች በሕዝብ ውስጥ ያለን ተቀባይነት የምናይበት ነው፡፡ የራሳችንን ቦታ ከልለን‹‹የእዚህ አካባቢ ድምፅ ነኝ!››እያልን ነው ያለነው፡፡በሰለጠነ መንገድ ሕዝቡ ይፈልገናል አይፈልገንም የሚለውን የምናይበት ምርጫ ነው፡፡

አሸንፎ የሚወጣው ፓርቲ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕጋዊና ቅቡል ይሆናል፡፡ ሌላው የተለያየ አካባቢ ያሉ ሕዝቦችን ፍላጎት የሚያንጸባርቁ ፓርቲዎች እድሉ ይኖራቸዋል፡፡ የተለያየ የሕዝብ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይኖረንም ይሆናል፡፡ 2013ዓ.ም ምርጫ ሀገራዊ ፋይዳ አለው ብለን እናስባለን፡፡ ምርጫው ፍጹም እንከን የለሽ ሆኖ ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን ጠቅላላ ያሟላል ብለን አንጠብቅም፡፡

*ኢዜማ ምርጫው ፍትሃዊ ነው ብሎ ለመቀበል ያስቀመጠው መመዘኛዎቹ ምንድን ናቸው?*

አራት መመዘኛዎችን አስቀምጠናል፡፡ ከአራቱ አንዱ ከጎደለ ምርጫው ፍትሃዊ አይደለም ብለን ለመደምደም እንገደደለሰን።ሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንደልባቸው በየቦታው መንቀሳቀስ እና ከሕዝብ ጋር ተገናኝተው ሃሳባቸውን መሸጥ አለባቸው፡፡ከምርጫው ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት ተፎካካሪ ፓርቲዎችን በእኩል ዓይን ማየት አለባቸው፡፡ ምርጫ ቦርድ ፍትሃዊ መሆን አለበት፡፡ መራጩ ሕዝብ ብመርጥ ይሄ ነገር ይደርስብኛል ብሎ ሳይፈራ እንዲመርጥ ሀገራዊ ድባቡ የሚያስፈራ መሆን የለበትም፡፡ ሕዝቡ የፈለገውን ከመረጠ በኋላ ቆጠራው በትክክለኛ መንገድ መቆጠር አለበት፡፡ የዚህ ዓይነት መመዘኛዎች ካልተሟሉ ፍትሃዊ ነው ልንል አንችልም፡፡ እነዚህ ከተሟሉ ደግሞ ሀገራችን ያለችበት አደገኛ ሁኔታ በመቀየር ወደ ተሻለ ነገር የሚቀይር በጠንካራ መሠረት ላይ ይዞ ሊሄድ የሚችል ሀገራዊ ሁኔታ ይፈጠራል ብለን እናምናለን፡፡ ይሄን አስቀምጠን የምርጫ ዝግጅት ጀምረናል፡፡ የምርጫ ስትራቴጂ ማኔጅመነት ሰባት ዘርፎች ያሉት ኮሚቴም አቋቁሟል፡፡

*ዘርፎቹ ምን ምን ናቸው?*

የምርጫ የሕዝብግንኙነት፣ የምርጫ ድርጅትጉዳይ፣ የእጩ ምልመላናድጋፍ፣ የምርጫ የፖሊሲ ማኒፌስቶ ፕሮግራም፣ የሀብትና ግብአት አሰባሰብ፣ የመንግሥት ጉዳዮች ዘርፍና የምርጫ ጽህፈት ቤት አገልግሎት ናቸው፡፡

*የምርጫ ማኔጅመንትስ ዋናው ሥራው ምንድን ነው?*

የምርጫ ማኔጅመነት የምርጫ ዘመቻ ቡድን የፌዴራል፣ የክልል፣የምርጫ ወረዳ የምርጫ ዘመቻ ቡድን አለ፡፡ ሥራው ለሦስት ተከፋፍሎ ነው ዘመቻ የሚደረገው፡፡እነዚህ ሦስት አካላት በራሳቸው የሚያደርጉት አለ፡፡ በብሔራዊ፣ በክልል እና በምርጫም ወረዳ እንዲሁም በሦስተኛ ወገን በምንጠራው በኩል የምርጫ ዘመቻ እናደርጋለን፡፡ እነዚህን ለማድረግ መመዘኛዎች አስቀምጠናል፡፡ ከመመዘኛዎቹ አንዱ በየደረጃው የሚገኘውን የሕዝቡን ችግር አጥንቶ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መፍትሔ ማዘጋጀት እና ለሕዝቡ ማድረስ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የምንወዳደርባቸው ቦታዎች ይሄን ሥራ መሸከም የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ሌላው እጩዎቻችን በምንወዳደርባቸው ምርጫ ወረዳዎች ላይ ብቃት ያላቸው፣ሥነ ምግባር ያላቸው፣ ተቀባይነት ያላቸውን ተመራጮች እያዘጋጀን ነው፡፡ በአራተኛ ደረጃ ምርጫው ከፍተኛ ወጪ ስለሚጠይቅ የገንዘብም ሆነ የቁስ ግብዓቶችን የማዘጋጀት ሂደት ላይ ነው የምንገኘው፡፡

*አሁን ካለው አንጻር ምርጫው ምን ያህል ዴሞክራሲያዊ ይሆናል ብሎ ኢዜማ ያምናል?*

እጅግ ውስብብ በሆነ ሀገር ላይ የሚደረግ ምርጫ ነው፡፡ መንግሥት በብዙ መልኩ የመንግሥትን መዋቅር ስለያዘ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች በተሻለ አማራጮች አሉት፡፡ ቢያንስ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሰው ጋር መድረስ መከልከል የለባቸውም፡፡ ሰው ጋር ደርሰው ሃሳባቸውን መሸጥ አለባቸው፡፡ ይሄ ካልተደረገ‹‹ምርጫው ዴሞክራሲያዊ ነው!››ልንል አንችልም፡፡ መንግሥት ምርጫ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ እስካለ ድረስ፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች የትም ቦታ ተንቀሳቀስው አማራጫቸውን የሚያስተዋውቁበትን መደላድል መፍጠር አለበት፡፡

*በሀገራችን ሀገራዊ ቀውስና ግጭቶች በየጊዜው እየተባባሱ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ወቅት የሀገር ህልውና ማስቀደም ሲገባ ኢዜማ ስለምርጫ ማሰቡ እና ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀሱ ተገቢ አይደለም ብለው የሚተቹ ወገኖች አሉ፡፡ ለዚህ ምላሻችሁ ምንድን ነው?*

ከሀገራዊ ምስቅልቅል ወደ ተሻለ ደረጃ መቀየር የሚቻልበት ብቸኛው አማራጭ ምርጫ ነው፡፡ ምርጫ ተደርጎ ቅቡልነት ያለው መንግሥት መጥቶ የተመረጠው መንግሥት ደግሞ ሕግ የሚያስከብረው ጠንካራ የሆነ የሕዝብ አቀባበልና ከልብ የመነጨ ሕዝባዊ ድጋፍ ሲኖረው ነው፡፡ይሄን ማድረግ የሚቻለው ፍትሃዊ የሆነ ምርጫ ተደርጎ ቅቡል የሆነ መንግሥት ሲኖር ነው፡፡ስለዚህ ምርጫ የሚደረገው ሀገር ለማዳን ነው፡፡ ይሄ ምርጫ ግዴታም ነው፡፡

*ከዚህ በፊት በአንዳንድ ክልሎች በመንግሥት መዋቅር አማካኝነት ለሀገር አቀፍ ምርጫ አስመራጭ እየመለመሉ እንደሚገኙ ኢዜማ ለምርጫ ቦርድ መግለጹ የዜጎች መድረክም መዘገቡ ይታወቃል፡፡ ቦርዱም ኢዜማ ላቀረበው አቤቱታ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ይሄን ስናይ ምርጫውን ተዓማኒ ነው ብሎ እንዴት ማመን ይቻላል?*

ቀደም ብዬ እንዳነሳሁልህ ምርጫውን ዴሞክራሲያው ነው ለማለት አራት ነገሮችን መሟላት ይገባቸዋል፡፡ መንግሥት እንደበፊቱ ዓይነት ምርጫ አደርጋለሁ ካለ ራሱን ችግር ውስጥ ይከታል፡፡ ይሄ ሕዝብ የበፊቱን ዓይነት ምርጫ የሚሸከምበት ምንም አይነት ነገር የለም፡፡ መንግሥት ለራሱ ሲል ችግር ውስጥ ላለመግባት ይሄን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ፍጹም ፍትሃዊ እንኳን ባይሆን ቅቡልነት ያለው ምርጫ ማድረግ ይገባዋል፡፡ በመንግሥት ሥር ምዝገባ እየተካሄደ ነው፡፡ ይሄን ምርጫ ቦርድን ጠይቀን ቦርዱም ይሄን ጉዳይ እንደማያውቀው ቦርዱ ቅጥሩን በራሱ መንገድ እንደሚያደርግ አሳውቆናል፡፡

*ኢዜማ፣ ‹‹የብልፅግና ተለጣፊ››ነው በሚል የሚሰነዘርበት ትችት በምርጫው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አይፈጥርበትም?*

የፖለቲካ ባህላችን ዛሬም አልተቀየረም፡፡ የተለመደው የፖለቲካ ሂደት መንግሥትን መተቸት ብቻ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ነገር እየተከታተሉ ጭቃ መወራወር፡፡ የእኛ ዋና ሥራ የሕዝብን ችግር አይቶና አጥንቶ መፍትሔ ማቅረብ ነው፡፡ገዢው ፓርቲ የትም እንድንንቀሳቀስ ይፍቀድልን እንጂ እኛ ያደረግነውን ዝግጅት ለሕዝቡ ሃሳባችንን አቅርበን ሕዝብ ይፈርዳል፡፡ሕዝቡ አማራጮቻችንን በሚገባ ከሰማና ካየ አይመርጠንም የሚል እሳቤ የለንም፡፡

መንግሥት ሕግ ለማስከበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደማንኛውም ባለድርሻ አካል እንደግፋለን፡፡ሀገሪቷ ውስብስብ ለውጥ ውስጥ መሆኗን እንረዳለን፡፡ ይሄ ለውጥ ምርጫ ተደርጎ ጠንካራ መሠረት ላይ ሊቆም እንደሚገባ እናምናለን፡፡ከዛ ውጭ ሕዝቡ ተለጣፊ ናችሁ ይላል የሚለው በምን ደረጃ ተጣርቶ ነው?

*ኢዜማም ይሄን ሲባል (የብልፅግና ተለጣፊ) ምንም አይነት ምላሽ እየሰጠ አይደለም፡፡ ስለዚህም ዝምታው በሚባለው ተስማምቶ ነው የሚሉ አሉ፡፡*

ኢዜማ የተቋቋመው ለጉምጉምታ ምላሽ ለመስጠት አይደለም፡፡ አንድ ሀገር ላይ ፖለቲካ ፓርቲ ሲቋቋም የሕብረተሰቡን ችግር እፈታለሁ ብሎ ነው፡፡ ሲጀመርም ያንን ለማድረግ ዝግጅት አድርጎ ነው፡፡ ኢዜማም ያዘጋጀውን ለሕዝብ ማቅረብ አለበት እንጂ እንዲዚህ አይነት ነገሮች ማዳመጥና መመለስ የለበትም፡፡ ጊዜውም የለንም፡፡

*የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያወጣውን መስፈርት ያላሟሉ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ሰርዟል፡፡ቦርዱ የሰረዛቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ቦርዱ ባደረገው የማጣራ ትሂደት ቦርዱ የጠየቀውን የድጋፍ ፊርማ ላይ ውጤታቸው ከ35 በመቶ በታች የሆኑትን*

## አድራሻ


ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)


ታህሳስ 21 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

*መሆኑ አስታውቋል፡፡ መስፈርቱ ከግማሽ (ከ50 በመቶ)በታች ማድረጉ በተፅዕኖ ስር መሆኑን ያሳያል የሚሉ አካላት አሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የኢዜማ አተያይ ምን ይመስላል?*

ምርጫ ቦርድ የሚመለከተውን ራሱ ምላሽ መስጠት ይገባዋል፡፡ እኛ ግን በፌዴራል ደረጃ የሚችለውን ያህል እያደረገ እንደሆነ ይሰማናል፡፡ ለምንጠይቀው ጥያቄዎች መልስ እየሰጠን ይገኛል፡፡ ይሄ እየሆነ ያለው በፌዴራል ደረጃ ባለው ቦርድ ነው፡፡ በክልል ደረጃ የሚኖረው ቦርድ በፍትሃዊነት ካላስተናገደ ከባድ ነው፡፡ ወደ ፊት ወደ ወረዳዎች ሲያወርዱት የምናየው ይሆናል፡፡ ዋናው ጉዳይ ያለው ታች ላይ ሕዝቡ ድምጽ የሚሰጥበት ጋር ነው፡፡ ማዕከል ላይ ያለው ቦርድ ታች ላይ ካልሰራ ችግር ውስጥ ነው የምንገባው፡፡ካስቀመጥነው መመዘኛ አንዱ ቦርዱ ፍትሃዊ ሆኖ ሁሉንም ተፎካካሪ እኩል ማስተናገድ አለበት የሚል ነው፡፡
ቦርዱም እንደ አዲስ የተዋቀረ ነው፡፡ የኮቪድ ወረርሽኝን በመሳሰሉ ችግሮች ውስጥ ነው ለመሥራት እየሞከረ ያለው፡፡አሁንም ደግሜ የምለው በማዕከል ደረጃ የሚችሉትን እያደረጉ ነው፡፡በክልል ደረጃ በገጠር የሚከወኑ ብዙ ሥራዎች አሉ፡፡ በእነዚህ ቦታዎች የምርጫ ቦርድ ሚና በጣም አስፈላጊ ነው፡፡እሱን ከገመገምን በኋላ ነው ስለ ምርጫ ቦርድ በልበ ሙሉነት መናገር የምንችለው፡፡

*ኢዜማ ምርጫው ፍትሃዊ አይደለም የሚለው ምን አይነት ጉድለት ሲያጋጥም ነው፡፡*

ከላይ የጠቀስኳቸው አራት መመዘኛዎች ሲጎድሉ ምርጫው ቅቡልነት የለውም፡፡ እንከን የለሽ ምርጫ አንጠብቅም፡፡ ልምዱም የለንም፡፡ የራሳችንም ሰዎች፣ ተቃዋሚዎችም ያጠፉ ይሆናል፡፡

*የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ምርጫ በአንድ ሳምንት ዘግይቶ ይካሄዳል፡፡ ምርጫው ላይ ሁለት ቦታ ሊመርጡ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ የሚሉ አሉ፡፡ እናንተ ይሄን እንዴት ትቀበሉታላችሁ?ውሳኔው ተፅዕኖ አይፈጥርባችሁም?*

እንደዚህ የሆነበት ምክንያት የፌዴራሉ ምርጫ በጊዜው የሚደረግ ሲሆን የከተማዎች ምርጫ ደግሞ በክፍለ ከተማዎች መደረጉና አንድ ሳምንት ምርጫ ቦርድ ለማስተካከል ስለሚስፈልገው ነው፡፡ ሌላ ቦታ የመረጠ ሰው ድጋሚ መጥቶ ይመርጣል ለሚለው ምርጫ ቦርድ ለምርጫ የተመዘገቡት ሰዎች ስም ዝርዝር ከአስር ቀን በፊት ይለጥፋል፡፡ የተለጠፉት ሰዎች ማንነት አይተን ማጣራት እንችላለን፡፡ የተባለውን ለመደገፍ ነው ብለን አናምንም፡፡ የክልል ምርጫ ተደርጎ ድጋሚ ምርጫ የሚደረገው በክፍለ ከተማ አከላል ነው፡፡አሁን የሚባለው ምክንያት አያሳምንም፡፡ ውሳኔውን ከተፅዕኖ አንጻር አናየውም፡፡ ከበስተጀርባው ክፉ እሳቤ እስከ ሌለው ድረስ ምርጫ ቦርድ የሚያመጣውን መቀበል አለብን፡፡

*ምርጫ ቦርድ ስለወሰነ ብቻ እናንተ አጣብቂኝ ውስጥ ቢከታችሁም ትቀበላላችሁ?*

አግባብ ያልሆነ ነገር አንቀበልም፡፡ ለምርጫ ብለን ደግሞ አግባብ ያልሆነ ነገር አንቀበልም፡፡ ፍትሃዊ እስከሆነና ፓርቲዎች ላይ አድሎ እስካልተፈጠረ ድረስ ጫና የሚፈጥርብን አሰራርም ቢሆን መቀበል አለብን፡፡ ቦርዱ ከአስር ቀን በፊት ስለሚለጥፍ በምርጫ ወረዳችን በተቻለው አቅም ለማጣራት እንጥራለን፡፡ አጣርተን ችግር ሲፈጠር አመልክተን የሚሰጡት ምላሽ ነው ፍትሃዊ ነው አይደለም የሚያስብለን፡፡

*በአዲስ አበባና በድሬዳዋ በሚደረገው ምርጫ የሕዝቡን ስጋት እንዲወገድ በምን ዓይነት መንገድ የማሳወቅና የመግለጽ ሥራ ትሰራላችሁ?*

እኛ የተረዳነውን ያህል ስለ አዲስ አበባም ሆነ ድሬዳዋ ሕዝብ ለመግለጽ ዝግጁ ነን፡፡ በምርጫ ወረዳም ስንደራጅ የተሻለ ደረጃ ስላለን በተቻ ለመጠን ለሕዝቡ መረጃዎችን ለማድረስ እየሞከርን ነው፡፡

*ኢዜማን ወክለው በምርጫው መሳተፍ የሚፈልጉ በምን መልኩ መሳተፍ ይቻላሉ?መስፈርቱስ ምን ይመስላል?*

በጥር 1/2 በሳምንቱ 8/9 ቀን 2013 ዓ.ም የእጩዎች ምርጫ እናደርጋለን፡፡ ኢዜማን ወክለው መወዳደር የሚፈልጉ የአባልነት ፎርም ሞልተው፣የስድስት ወር ወርኃዊ ክፍያ ከከፈሉ በኋላ መመዘኛዎችን አይተው መመዝገብ ይችላሉ፡፡ በመቀጠል በምርጫ ወረዳ ጉባኤ ይመረጣሉ፡፡ በወረዳው በሚሰጠው ድምፅ ሊያልፉም ሊወድቁም ይችላሉ፡፡ ትልቅ ዘመቻ እና ሥራ ያለው ምርጫ ወረዳ ላይ ነው፡፡

*በሚደረገው ምርጫ እምነት በማጣት ወይም ከዚህ ቀደም ባለው ተሞክሮ መነሾ በማድረግ ካርድ አንወስድም፣ ምርጫ አንመርጥም ለሚሉ ምን ይላሉ?*

ይሄ ታሪካዊና ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ምርጫ ነው፡፡ ሀገሪቷ ችግር ውስጥ እንዳለች እያየነውነው፡፡ ሀገራችን ከዚህ አደገኛ ሁኔታ መሻገር አለባት፡፡ ሕዝቡ የመረጠው መንግሥት የሕዝብ ውክልና ያለው በመሆኑ መንግሥት ከዚህ ችግር ሊያወጣው ይችላል፡፡ የመረጥከውን መንግሥት የሚወስነውን ውሳኔ ትቀበለዋለህ፣ታዳምጠዋለህ፣ታግዘዋለህ...ስለዚህ ይሄ ምርጫ ካለንበት ማጥ የሚያወጣን ስለሆነ ካርድ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ከምንም በላይ ለእኛ አባላት ደጋፊዎች ያዘጋጀነው የሥነምግባር ሰነድ አለ፡፡ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዕጩዎች፣ ደጋፊዎች አባላት በዛ የምርጫ ሰነድ ነው የሚዳኙት፡፡ ይሄ ምርጫ ከፍተኛ ፋይዳ አለው ብለን ነው የምናምነው፡፡
ለሌሎች ፓርቲዎች ጥሪ የማደርገው ይሄ ምርጫ እንደቀላል ሳያዩት ለአባሎቻቸው፣ለደጋፊዎቻቸው እና አመራሮቻቸው የሚመሩበት የስነ ምግባር ደንብ ሊያዘገጁ እንደሚገባ እና ጠንክረው በማስፈፀም መጪው ሀገራዊ ምርጫ ለሚኖረው ሀገራዊ ፋይዳ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ነው።

*በእኔ በኩል ጥያቄዎቼን አገባድጃለሁ፡፡ የሚያስተላልፉት መልእክት ካሎት እድሉን ልስጥዎት?*

መጪው ምርጫ ሀገር እናሻግርበታለን ብለን የምናስብበት ምርጫ ነው፡፡እድሜያቸው ለመምረጥ የደረሱ ዜጎችና የመምረጥ መብታቸው በሕግ ያልተገደበባቸው ዜጎች በሙላ በመጪው ምርጫ በመምረጥ መሳተፍ አለባቸው፡፡

*ለቃለምልልሱ ፍቃደኛ ስለሆኑ በዜጎች መድረክ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡*

እኔም አመሰግናለሁ፡፡



# ነፃ ሀሳብ

ማሳሰቢያ፡- ይህ ፅሁፍ የፀሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚወክለው!

## የምርጫ ጊዜ ሰሌዳ እና የሁለት ቀን ምርጫ




የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 6ኛውን ሀገራዊ ምርጫ ለማድረግ ለሁለተኛ ጊዜ የጊዜ ሰሌዳ ባሳለፍነው አርብ ታኅሣሥ 16 ቀን 2013 ዓ.ም ይፋ አድርጓል። ከዚህ ቀደም ምርጫውን ነሐሴ 23 ቀን 2012 ዓ.ም ለማድረግ የጊዜ ሰሌዳ አውጥቶ እንደነበር የሚታወስ ነው። መጋቢት 4 ቀን 2012 ዓ.ም የኮሮና ቫይረስ ያለበት የጃፓን ዜግነት ያለው ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ መገኘቱን ተከትሎ መንግሥት ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ እና ሰዎች በብዛት አንድ ቦታ ተሰብስበው የሚሠሩ ሥራዎች ላይ ባስቀመጠው ገደብ ተከትሎ ቦርዱ ሥራዎቹን ማቆሙን አስታውቆ ነበር። ቆየት ብሎም የእንቅስቃሴ እና የሥራ ገደቡ ነሐሴ 23 ቀን ምርጫ ለማድረግ የተቀመጠውን የጊዜ ሰሌዳ ማሳካት አያስችለኝም ማለቱ ይታወሳል። ለሁለተኛ ጊዜ ይፋ የተደረገው የምርጫ ሰሌዳ ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ላይ ያሉኝን ምልከታዎች በዚህ ጽሑፍ ለማንሳት እሞክራለሁ።

ታኅሣሥ 16 ይፋ የተደረገው የ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ላይ የአዲስ አበባ እና ድሬደዋ የከተማ ምክር ቤት ምርጫ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚደረገው የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት እና በ10ሩ ክልሎች ከሚካሄደው የክልል ምክር ቤት ምርጫ በአንድ ሳምንት ዘግይቶ እንደሚደረግ ማሳወቁ ቀላል ለማይባሉ ሰዎች ግርታ እና የስጋት ምንጭ ሆኗል። በዚህ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ነዋሪዎች ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር በአንድ ቀን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወካዮቻቸውን ሲመርጡ በከተማ ምክር ቤት የሚወክሏቸውን ሰዎች ግን ከአንድ ሳምንት በኋላ ሰኔ 5 ቀን 2013 ዓ.ም የሚመርጡ ይሆናል ማለት ነው። ከአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም የክልል ምክር ቤትም ወካዮቻቸውን ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም አድርገው ይጨርሳሉ ማለት ነው።

### አዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከሌሎቹ በምን ተለዩ?

በሁለቱ ከተሞች ምርጫው በአንድ ቀን ተካሂዶ እንዳይጠናቀቅ እንቅፋት የሆነው በከተማዎቹ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለከተማው ምክር ቤት ውድድር የሚካሄድባቸው የምርጫ ክልሎች (የምርጫ ወረዳዎች) የተለያዩ መሆናቸው ነው።በአዲስ አበባ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እያንዳንዳቸው 1 ተወካይ አሸንፎ/ፋ የሚወከልባቸው/የምትወከልባቸው 23 ምርጫ ወረዳዎች ውድድር ሲደረግ ለከተማው ምክር ቤት ግን በ12 ተወካዮች ከሚወከለው አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ውጪ 9ኙ ክፍለ ከተማዎች 14 ተወካዮች የሚመረጡበት 10ሩ ክፍለ ከተሞች እንደ ምርጫ ወረዳ ተቆጥረው ውድድር ይካሄድባቸዋል።

ለምሳሌ ኢዜማ በአዲስ አበባ በ23 ምርጫ ወረዳዎች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወዳደሩ 23 ዕጩዎችን የሚያቀርብ ሲሆን ለከተማው ምክር ቤት ደግሞ በ10 ምርጫ ወረዳዎች የሚወዳደሩ በአጠቃላይ 138 ዕጩዎችን (14 ዕጩዎች በዘጠኙ ክፍለ ከተማዎች እና የአቃቂ ቃሊቲ 12 ዕጩዎች) ያቀርባል ማለት ነው።

በድሬደዋም በተመሳሳይ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውድድር የሚደረግባቸው 2 የምርጫ

ወረዳዎች እና ለከተማው ምክር ቤት ውድድር የሚደረግባቸው 47 የምርጫ ወረዳዎች አሉ።
ከአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ውጪ በሌሎች ክልሎች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ውድድር የሚደረግባቸው የምርጫ ወረዳዎች ቁጥርም ሆነ ወሰናቸው አንድ ዓይነት ነው (በአማራ ክልል የምርጫ ወረዳዎቹ በክልሉ ምክር ቤት የሚወከሉበት ቁጥር የሁሉም እኩል አይደለም)።

## ይህ ለምን ሆነ? ከመቼ ጀምሮ?

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መልሶ ከተቋቋመ በኋላ ምርጫ ለማድረግ ከነበረው የጊዜ ጥበት እና የሕዝብ ቆጠራ ካለመካሄዱ ጋር ተያይዞ የምርጫ ክልሎችን እንደገና ለማዋቀር እና 6ኛውን ሀገራዊ ምርጫ እንደ አዲስ በተዋቀሩት የምርጫ ክልሎች ለማድረግ እንደማይችል፤በዚህም ምክንያት በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ የምርጫ ክልሎች (ወረዳዎች) ከዚህ ቀደም የመጨረሻ ምርጫ ሲካሄድ በነበሩበት ሆነው እንደሚካሄድ አሳውቆ ነበር።

የ1997 ዓ፠ም ድህረ ምርጫ ችግርን ተከትሎ አዲስ አበባ ለ3 ዓመት በባላደራ አስተዳደር ከተመራች በኋላ በ2000 ዓ፠ም እና በኋላም ከዚህ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ በአዲስ አበባ ተደረገ በተባለው የ2005 ዓ፠ም የከተማ ምክር ቤት ምርጫ ጥቅም ላይ የዋሉት የምርጫ ወረዳዎች እንደ በፊቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውድድር የሚደረግባቸው 23 የምርጫ ወረዳዎች ሳይሆኑ ከ1995 ዓ፠ም ጀምሮ ሥራ ላይ የዋሉት የአስተዳደር 10 ክፍለ ከተማዎች ነበሩ።በዚህ መሰረት በድሮው አከላለል በ23 ምርጫ ወረዳዎች እያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ በ6 ተወካዮች ይወከልበት የነበረው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት (23*6=138) በ2005ቱ ምርጫ አንዱ ክፍለ ከተማ በ12 ሰው ተወክሎ ዘጠኙ ደግሞ በ14 ሰዎች እንዲወከሉ ተደረገ[(9*14)+12]=138።

## ከክልል እና ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውድድር የሚደረግባቸው የምርጫ ወረዳዎች መለያየት ምርጫውን በአንድ ቀን ለማካሄድ የሚፈጥረው ተግዳሮት ምንድነው?

ይህን ለማስረዳት እኔ የኢዜማ አባል የሆንኩበትን የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 8ን እንይ።ምርጫ ወረዳ 8 አዲስ አበባበ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ከምትወከልባቸው 23 መቀመጫዎች ለአንደኛው ውድድር የሚደረግበት ምርጫ ወረዳ ነው።ይህ ምርጫ ወረዳ በክፍለ ከተማ (በ2005 ምርጫ የምርጫ ወረዳ የነበሩት) አወቃቀር ከተመለከትነው 3 ክፍለ ከተማዎች ውስጥ ይገኛል - አዲስ ከተማ፣ኮልፌ ቀራኒዮ እና ጉለሌ።በዚህ ምክንያት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአንድ ምርጫ ወረዳ ድምፅ ሰጥተው አንድ ተወካይ የመረጡት የምርጫ ወረዳ 8 ነዋሪዎች ለከተማው ምክር ቤት በሚደረገው ምርጫ የሚሳተፉት ግን በ3 የተለያየ የምርጫ ወረዳ ሊሆን ይችላል ማለት ነው።
በምሳሌ ለማስረዳት አንድ አስኮ አካባቢ የምትኖር የአዲስ አበባ ነዋሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምትወክላትን/የሚወክላትን ሰው በቀድሞ ወረዳ 8 ስር ከሚገኙት ከሽጎሌ እና አዲሱ ሚካኤል አካባቢ ነዋሪዎች ጋር አንድ ላይ ስትመርጥ በከተማው ምክር ቤት የሚወክሏትን ሰዎች ደግሞ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ስር ከሚገኙት የአየር ጤና እና ኮልፌ አካባቢ ሰዎች ጋር ትመርጣለች ማለት ነው።

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤት ውድድር የሚካሄድባቸው የምርጫ ወረዳዎች አንድ ዓይነት በሆኑባቸው አካባቢዎች (በ1997 ምርጫ በመላው ሀገራችን አንድ ዓይነት ነበር) ከምርጫ ቦርድ የሚጠበቀው በየምርጫ ጣቢያው ሁለት የተለያዩ የምርጫ መስጫ ወረቀቶች (አንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወዳደሩ እና አንድ ለክልል ምክር ቤት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን የያዘ) እንዲሁም ሁለት የተለያዩ የምርጫ ኮሮጆዎች ማዘጋጀት ነው።ለሁለቱ ምክር ቤቶች ውድድር የሚደረግባቸው የምርጫ ወረዳዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ሲደበላለቁ ግን ይህን ማድረግ አይቻልም።
ይህ የምርጫ ወረዳ (constituency) መደበላለቅን ማስተካከል 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ እንዳለፈ ግንባር ቀደም የቦርዱ ሥራ መሆን ይገባዋል።

## ስጋት እና መፍትሄ?

በሁለቱ ከተማዎች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤት ምርጫ በአንድ ቀን አለመደረጉ ቀድመው የምርጫውን ውጤት ለመጠምዘዝ የተዘጋጁ ቡድኖችን ይጠቅማል የሚል ስጋት የገባቸው ሰዎች አሉ።

በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በተለያየ ጊዜ ከነዋሪነት መታወቂያ ካርድ ጋር ተያይዞ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን በማስታወስ ግንቦት 28 ሌላ ቦታ የመረጡ ሰዎች ሰኔ 5 አዲስ አበባ መጥተው መርጠው የከተማው ምክር ቤት ምርጫውን ውጤት ያዛንፋሉ የሚል ስጋት የሚያነሱ ሰዎች አሉ።
እንዲህ ዓይነት ስጋት የገባቸው ነዋሪዎች/ የፖለቲካ ድርጅቶች ስጋታቸውን የሚቀንስላቸው የምርጫ ቦርዱ አሠራር አለ። ቦርዱ ለምርጫው ያዘጋጃቸውን ቁሳቁሶች ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ባስጎበኘበት ወቅት እንዳስረዳው እና አሁንም በጊዜ ሰሌዳው ውስጥ እንደተካተተው እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ለመምረጥ የተመዘገቡ ሰዎች መረጃ ምዝገባው ካለቀ በኋላ ለ10 ቀን (ከመጋቢት 22 - ሚያዝያ 1 ድረስ) ለሕዝብ ይፋ ይሆናል። በእነዚህ 10 ቀን ውስጥ እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ላይ የተመዘገቡት ሰዎች (በምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ አንቀጽ 15 (6) መሰረት በአንድ ምርጫ ጣቢያ መመዝገብ የሚችለው ከፍተኛ የመራጭ ቁጥር 1,500 ነው።) እነማን እንደሆኑ እና ሲመዘገቡ የተጠቀሙት አድራሻ ይፋ ይደረጋል።

ምርጫው ነፃ፣ ፍትሃዊ እናዴሞክራሲያዊ መሆኑ የሚያሳስበን የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የምንመድባቸው ታዛቢዎች ይህን መዝገብ በደንብ በመመርመር አጠራጣሪ መረጃዎችን (ለምሳሌ በአንድ የቤት ቁጥር ከፍተኛ ቁጥር መራጭ የተመዘገበበትን) የማጣራት ኃላፊነት ልንወስድ ይገባል። በተመሳሳይ ምርጫው ፍትሃዊ መሆን እንዳለበት የሚያምን እያንዳንዱ ዜጋ ቢያንስ በራሱ ቤት ቁጥር የተመዘገቡትን መራጮች ይፋ ከሚደረገው የመራጮች መዝገብ በማጣራት ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካለ ይህንኑ ለቦርዱ እና ለሚመለከታቸው አካላት ይፋ ማድረግ ይጠበቅበታል።
ኢዜማ በሚወዳደርባቸው የምርጫ ወረዳዎች ስር በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች በእያንዳንዳቸው የሚመድባቸው ሁለት ሁለት የኢዜማ ምርጫ ታዛቢዎች ይህንን የማጣራት ሥራ ለመሥራት ዕቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።





# ኢዜማ፣ በባህር ዳር ለሚገኙ አባላቶቹ የእጩ መመልመያ መስፈርቱን የሚዳስስ ስልጠና ሰጠ

ታኅሣሥ 21 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎቹ መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የባህር ዳር ምርጫ ወረዳ እሁድ ታኅሣሥ 18 ቀን 2013 ዓ.ም እጩ ተወዳዳሪዎች ምልመላ መስፈርትን በተመለከተ ለአባላቱ ስልጠና መስጠቱን የኢዜማ የባህር ዳር ምርጫ ወረዳ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ መንግሥቱ አማረ ለዜጎች መድረክ ገለፁ::

የኢዜማ እጩ ምልመላና ድጋፍ ኮሚቴ ባወጣው መስፈርት መሰረት እስከ ጥር 09 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ በየወረዳው ሊወዳደሩ የሚችሉ የክልል ምክር ቤት ተወዳዳሪዎችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወዳዳሪ እጩዎችን ማቅረብ እንደሚገባ በስልጠናው ወቅት ማብራሪያ መቅረቡን ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ጠቁመዋል:: ባህር ዳር የክልሉ ርዕሰ መዲና ከመሆኗ አንፃርም ባህር ዳርን ሊወክሉ የሚችሉ እጩዎችን መመልመልና ማወዳደር እንደሚገባ በስልጠናው ወቅት እንደተገለፀ የጠቀሱት ኃላፊው፣ የኢዜማ የእጩ መመልመያ መስፈርት ምን እንደሚመስል አባላት ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉን ገልፀዋል::



በስልጠናው ላይ ባህር ዳር ከተማ ላይም ሆነ ክልሉ ላይ እጩ ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች አቅም ያላቸው፣ በሕዝብ ተቀባይነት ያላቸው፣ ቢመረጡ ሕዝብን ሊያገለግሉ የሚችሉ ሰዎች መሆን እንደሚገባቸው የተገለፀ ሲሆን፤ ለዚህም ሲባል በስፋት ሥራ መሰራት እንዳለበት በአባላት ዘንድ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል:: በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረትም መስፈርቱን የሚያሟሉ ዜጎች ኢዜማን ወክለው ምርጫ እንዲወዳደሩ ጥሪ ቀርቧል::

ስልጠናው ከመጠናቀቁ አስቀድሞም በተጓደለው የአስመራጭ ኮሚቴ አባል ምትክ የአስመራጭ ኮሚቴ ምርጫ ተደርጎ አዲስ አባል መመረጥ መቻሉን የገለፁት፤ የምርጫ ወረዳው ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣ አስመራጭ ኮሚቴው እጩ ሆነው ለውድድር የቀረቡትን ሰዎች ከለየ በኋላ የወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ በሚሰጠው ድምፅ ኢዜማን ወክሎ ምርጫ የሚወዳደሩ እጩዎች እንደሚታወቁ አስታውቀዋል::

# ምርጫ ወረዳ 17 6ኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ አስመልክቶ የአባላት ሚና ምን ሊሆን እንደሚገባ ውይይት አካሄደ

ታኅሣሥ 21 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 17 የአባላቱን 8ኛ መደበኛ ጉባኤ እሁድ ታኅሣሥ 18 ቀን 2013 ዓ.ም ማካሄዱን የምርጫ ወረዳው ሊቀመንበር ኤፍሬም ሰለሞን ለዜጎች መድረክ ገለፁ::

የጉባኤው አብይ አላማም፣ በያዝነው ዓመት በሚካሄደው 6ኛው ሀገር አቀፉ ምርጫ ላይ አባላት ሊኖራቸው ስለሚገባቸው ሚና ላይ መምከር እንደነበር ሊቀመንበሩ አስረድተዋል:: ይህኛውን ጉባኤ ከማካሄዳቸው በፊትም ወረዳቸው እጩ ሆኖ ከሚያቀርባቸው ተወዳዳሪዎች ምን እንደሚጠበቅ ለማስረዳት ውይይት ማካሄዱን ያስታወሱት ሊቀመንበሩ፣ በወቅቱ ወደ 300ሺህ ብር ያህል ገንዘብ መሰብሰብ መቻላቸውንም አስታውሰዋል :: ወረዳቸው ባሳለፍነው እሁድ ታኅሣሥ 18 ቀን 2013 ዓ.ም ያካሄው ጉባኤ ከምርጫው ጋር በተገናኘ ከአባላት ምን እንደሚጠበቅ ለማስረዳት የተደረገ መሆኑን ያወሱት ሊቀመንበሩ ኤፍሬም ሰለሞን፣ እጩዎችን ከመመልመል፣ ታዛቢዎችን ከማዘጋጀትና ከመሳሰሉት ጉዳዮች የአባላት ሚና ምን መምሰል እንዳለበት ውይይት ማድረጋቸውን አስረድተዋል:: ኢዜማ ለምርጫ እያደረገው ያለው ዝግጅት ምን ይመስላል? የሚለውን ግንዛቤ ለማስጨበጥ የኢዜማ የእጩዎች ድጋፍና ምልመላ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኢዮብ መሳፍንት፣ ለጉባኤው ተሳታፊዎች ገለፃ ማድረጋቸውን ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል::

በጉባኤው ላይ የኢዜማ ከፍተኛ አመራሮች የሆኑት መሪው ብርሀኑ ነጋ፣ ምክትል መሪው አንዷለም አራጌና ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ ታዳሚ እንደነበሩ የጠቆሙት ኤፍሬም ሰለሞን፣ የኢዜማ ከፍተኛ አመራሮች ምርጫ ወረዳ 17 ላይ ተስፋ እንደሚጥሉበት መናገራቸውንና ኢዜማ ከሚመካባቸው ወረዳዎች መሀል አንዱ ነው ማለታቸውን ጠቁመዋል:: ይህም ለአባላቱ ከፍተኛ የሞራል ስንቅ እንደሚሆን ገልፀዋል::

የቀበሌ አደረጃጀታቸውን መፈተሻቸውን የገለፁት የምርጫ ወረዳው ሊቀመንበር፣ በቀበሌ

አደረጃጀቶቻቸው ላይ የተወሰነ ሪፎርም ማድረጋቸውንና ደከም ብለው በተገኙ የቀበሌ አደረጃጀቶች ላይ የአመራር ለውጥ ማድረጋቸውን አስረድተዋል፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ከቀበሌዎቹ አባላት ጋር በመነጋገር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በምርጫ ወረዳቸውም 15 ያህል ቀበሌዎች መኖራቸውን የጠቀሱት ሊቀመንበሩ፣ የየቀበሌው ተጠሪዎች ከአባላት ጋር እንዲተዋወቁ ማድረጋቸውንና አዳዲስ የቀበሌ አመራሮች መመረጣቸውን ጠቁመዋል፡፡

ጉባኤው ሰፊ ውይይት የተደረገበት፣ በምርጫ ዙሪያ ኢዜማ እያደረገ ያለው ዝግጅት አባላት ግንዛቤ ያገኙበት፣ የቀበሌ አደረጃጀቶቻቸውን እንዲያከብሩና አብረዋቸው እንዲሰሩ ማሳሰቢያ የተሰጠበትና አዳዲስ የቀበሌ አመራሮች በመምረጥ ወደኋላ የቀሩት ቀበሌዎች ላይ የሪፎርም ሥራ የተሰራበት ነበር ሲሉ የምርጫ ወረዳው ሊቀመንበር ገልፀዋል፡፡

# ኢዜማ፣ በጤና፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በሥርዓተ ፆታ እና በሠራተኛና ሙያ ማኅበራት ረቂቅ ፖሊሲዎቹ ላይ ውይይት አደረገ

ታኅሣሥ 21 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ባሳለፍነው እሁድ ታኅሣሥ 18 ቀን 2013 ዓ.ም በዋና ጽህፈት ቤቱ በመስፍን ወልደማሪያም አዳራሽ በአራት የፖሊሲ ሰነዶቹ ላይ ውይይት አካሄደ፡፡

ውይይት የተካሄደባቸው የፖሊሲ ሰነዶች የጤና፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የሥርዓተ ፆታ እና የሠራተኛና የሙያ ማኅበራት ፖሊሲዎች ናቸው፡፡ ለውይይት በቀረቡት ረቂቅ የፖሊሲ ሰነዶች ላይ የፓርቲው ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላቶችና በፖሊሲ ዝግጅቱ ላይ ሚና የነበራቸው ባለሙያዎች ውይይት አካሄደዋል፡፡

መንግሥት በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የሕክምና ዘርፉን ሙያተኞች የሚመሩበት እድልን በማጥበቡ የሕክምና ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩን ያስታወሱት፤ የኢዜማ የፖሊሲ አስተባባሪ አማን ይኹን ረዳ፣ አርሶ አደሩ፣ አካል ጉዳተኛው፣ ሀብታሙንም ሆነ ድሀውን የማይለይ የጤና አገልግሎትን ታሳቢ ያደረገ የጤና ሥርዓትን የሚገነባ የጤና ፖሊሲ ኢዜማ ማዘጋጀቱን ለዜጎች መድረክ አስረድተዋል፡፡ ‹‹ጤና መብት ነው፤ የሀብታም ልዩ ጥቅም አይደለም›› ያሉት የፖሊሲ አስተባባሪው ባለሙያዎችን አሳትፈው፣ ዓለም አቀፍ ልምዶችን ቀምረው፣ የሀገሪቱንም ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት በመከተት የጤና ፖሊሲያቸውን መቅረፅ መቻላቸውን ጠቁመዋል፡፡

የአካል ጉዳተኞች ፖሊሲያቸውን በሚመለከት የፖሊሲ አስተባባሪው ሲያስረዱም ‹‹የሚመች ሀገር ለሁሉም ኢትዮጵያዊ›› ስንል አካል ጉዳተኞችን ጥለን ሌላውን አንጠልጥለን አይደለም ብለዋል፡፡ አካል ጉዳተኞች በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት የሚሳተፉበትና የሚጠቀሙበት እድል ማሳነስ እንደማይገባ አስረድተዋል፡፡ አካል ጉዳተኞች ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሠራሽ ምክንያቶች የተነሳ የተሳትፎ አድማሳቸውን ከሚያጠቡ ችግሮች ጋር እየተጋፈጡ እንዳለ የጠቀሱት የፖሊሲ አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ፣ በኢትዮጵያ 70 ከመቶ በላይ የሚሆኑ አካል ጉዳተኞች በከፋ ድህነት ውስጥ እንደሚኖሩ ጥናቶች እንደሚጠቁም ገልፀው፤ አካል ጉዳተኝነታቸው ለበርካታ ችግሮች ተጋላጭ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው አስረድተዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች፣ መብታቸው፣ ጥቅማቸው፣ ክብራቸው ተጠብቆ ለሀገር ልማት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ እንዲጎለብትና ቁጥራቸውን የሚመጥን የፖለቲካ ውክልና እንዲኖራቸውና በችሎታቸው የተመቻቸ የኢኮኖሚና የነቃ ማኅበራዊ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ የመሠረተ ልማት አቅርቦትም ሆነ መሠረታዊ አገልግሎቶች መመቻቸት እንዳለባቸው ጠቅሰዋል፡፡ ‹‹ሁሉም ኢትዮጵያዊ በክብር መኖር አለበት ስንል በሀገራችን የሚገኙ 20 ሚሊዮን አካል ጉዳተኞችን ዘንግተን አይደለም›› ያሉት የፖሊሲ አስተባባሪው የአካል ጉዳተኞችን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚረዳ ፖሊስ ፓርቲያቸው መቅረፁን ጠቁመዋል፡፡



የኢዜማ ዜና
ዜናዎች

‹‹የአካል ጉዳተኞችን ፖሊሲ በመቅረፅ ሂደት ውስጥ አካል ጉዳተኞችን አሳትፋችኋል?›› በሚል ከዜጎች መድረክ ለተነሳላቸው ጥያቄ የፖሊሲ አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ ሲመልሱም ‹‹እኛ እናውቅላችኋለን፤ ችግራችሁ ይሄ ነው ልንል አንፈልግም ፡፡ አካል ጉዳተኞን ሰብስበን ጥያቄዎቻቸውን በደንብ አደራጅተን ለጥያቄዎቻቸው መልስ የሚሰጥ የዘመናት ትግላቸውን በአንድ ምዕራፍ ወደፊት የሚያመጣ ፖሊሲ ነው ያዘጋጀነው፡ ፡ ፖሊሲውም በአካል ጉዳተኞች ነው የተዘጋጀው፡፡ በቀረፃው ሂደትም በተለያዩ ተቋማት የሚሠሩ አካል ጉዳተኞችም ፖሊሲው ላይ ሀሳብ እንዲሰጡበት በማድረግ ማሻሻያ አድርገንበታል›› በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

‹‹ኢዜማ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ነው›› ያሉት የፖሊሲ አስተባባሪው፣ አካል ጉዳተኞች በአካል ጉዳተኞች ፖሊሲ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ፖሊሲዎቻቸው ላይም እንዲሳተፉ ፓርቲያቸው እድሉን እንዳመቻቸ ጠቅሰዋል፡፡ ለምርጫ እጩ ሆኖ ለመቅረብም እድሉ የተመቻቸ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የሥርዓተ ፆታ ፖሊሲያቸውን በሚመለከት ለዜጎች መድረክ ማብራሪያ የሰጡት የፖሊሲ አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸውን አስታውሰው፣ ፓርቲያቸው ማኅበራዊ ተሳትፎን እናስፍን ብሎ ሲነሳ የሴቶችን የነቃ ተሳትፎ የሚያጎለብት ሀገራዊ ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው ብሎ እንደሚያምን አስረድተዋል፡፡ ሴቶች ላይ ተደራራቢ ጫና እንዳለ የጠቀሱት የፖሊሲ አስተባባሪው፣ ይህንንም ማስተካከል እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ ሴቶች ቁጥራቸውን የሚመጥን የፖለቲካ ውክልና ሊያገኙ የሚችሉበትን እድል ማመቻቸትን አላማው ያደረገ ፖሊሲ ፓርቲያቸው መቅረፅ መቻሉን አውስተዋል፡፡ ታኅሣሥ 18 ቀን 2013 ዓ.ም በተካሄደው የፖሊሲ ውይይት ላይ በስተመጨረሻ የቀረበው የሠራተኛና ሙያ ማኅበራት ፖሊሲ ነው፡፡ የዚህ ፖሊሲ ጥቅል አላማ ምን እንደሆነ ዜጎች መድረክ ጥያቄ ያቀረበላቸው የፖሊሲ አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ፣ መሠረታዊ ፍላቶችን ለማሟላት የማያስችል ክፍያ ለሠራተኛው እየተከፈለ ያለ ሀገራዊ ሁኔታ መኖሩን አስታውሰው፤ እውቀት፣ ክህሎትና የአመራር ብቃትን የሚያሳድጉ እድሎች ስላልተመቻቹ ሠራተኛው ምርታማነቱ ዝቅተኛ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በዚህ የተነሳም ዜጎች ለሀገር እድገት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ አናሳ መሆኑንና ሠራተኛውም ሆነ አሰሪው ተጠቃሚ ያልሆነበት ሥርዓት እንዳለ ተናግረዋል፡፡

የሠራተኛና ሙያ ማኅበራት ፖሊሲው ሙያ ማኅበራት እንዲጠናከሩ መንግሥት ምንድነው ማድረግ ያለበት? ሠራተኛው ጥቅሙ፣ መብቱ፣ ክብሩ እንዲጠበቅና ለሀገር ማበርከት ያለበት አስተዋፅኦ ለማሳደግ ምንድነው መደረግ ያለበት? የሚለውን በስፋት ፈትሾ የኢዜማን አማራጭ መፍትሔዎች የሚዳስስ ፖሊሲ እንደሆነ የፖሊሲ አስተባባሪው አስረድተዋል፡ ፡

ኢዜማ የኢትዮጵያን ሕዝብ መሰረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳሉ ያላቸውን ከ40 በላይ ፖሊሲዎች በባለሙያዎች ሲያዘጋጅ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ ሲሆን እስካሁን 16 ፖሊሲዎችን ለባለድርሻዎች ውይይት አቅርቧል። በቀሪዎቹ ፖሊሲዎች ላይም የተለያዩ የኅብረተሰብ ወኪሎችንና ባለድርሻዎችን ማወያየቱ የሚቀጥል ሲሆን፣ በያዝነው ሳምንትም የስነ ሕዝብ እና የአደጋ መከላከል ቅነሳና አስተዳደር ፖሊሲዎቹን ለውይይት የሚያቀርብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፓርቲው፣ ፖሊሲዎቹን እያካሄዳቸው ባሉ ተከታታይ ውይይቶች ላይ በውይይቱ የሚያገኛቸውን አስተያየቶች ካካተተ በኋላ እና በፓርቲው ኮንፈረንስ የኢዜማ ፖሊሲ ተብለው ከፀደቁ በኋላ ለሕዝብ ይፋ የሚያደርጋቸው ይሆናል፡፡

